ውድ አንባቢ፥

በዚችው ትንሽ መጽሐፍ የሚከተሉትን ሁሉ ታገኛለህ፡-

(1.) ወደ ዓለም ሊመጣ ያለውን መሢሕ አስመልክተው ስለ ልደቱ፥ ስለ ሞቱና ስለሚቀዳጀው ክብር ሁሉ ለተነገሩ አንዳንድ መሠረታዊ ትንቢቶች፥ በመጽሐፍ ቅዱስ በቶራኽና ዘቡር የሠፈሩ ማጣቀሻ ጽሑፎችን፥

(2.) ስለ መሢሑ ሲነገሩ የነበሩ ትንቢቶች ሁሉ በኢየሱስ መፈጸማቸውን የሚያበስሩ ጥቂት የኢንጅል(የአዲስ ኪዳን) ጥቅሶችን፥

(3.) ቁርአን በተደጋጋሚ መሢሑ ኢየሱስ! በማለት የጠቃቀሳቸውን።

መጽሐፉን ካነበብክ በኋላ የምትረዳቸው ዐበይት ቁም ነገሮች ይኖራሉ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር መሢሑን ለምን ወደ ዓለም እንደላከው ታስተውላለህ። በተጨማሪም መሢሑ ኢየሱስን ላመኑ ሁሉ እግዚአብሔር ሊያደርግላቸው ያለውን ፈቃድ ታጤናለህ።

«የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹ የተወሰዱት ከአሮጌው ትርጉም ነው።»

«የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት በ38 ኛው ዘመን ከታተመው የቁርአን መጽሐፍ ነው።»

## <u>የመሢሑ መወለድ በነቢያት በኩል በቶራኽና በዘቡር አስቀድሞ ተነግሮ ነበር።</u>

ከሴት ዘር ይመጣል
(ኦሪት ዘፍጥረት 3፡ 15)።

የአብርሃም ዘር ይሆናል
(ኦሪት ዘፍጥረት 22፡ 18)።
(2000 ዓ.ዓ)

የዳዊት ዘር ይሆናል
መዝሙረ ዳዊት (89)፡ 35-37)።
(1000 ዓ.ዓ)

ከድንግል ይወለዳል
(ኢሳይያስ 7፡ 17)
(700 ዓ.ዓ.)

በቤተልሔም ይወለዳል
(ሚክያስ 5፡ 2)።
(700 ዓ.ዓ)

## <u>የመሢሑ መወለድ በኢንጅል ውስጥ የተመዘገበ ነው</u>

«የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። <u>እናቱ ማርያም</u> ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ <u>ሳይገናኙ</u> <u>ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች</u>። ...እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥... የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥» (ማቴዎስ 1፡ 18፥22)።

«<u>የዳዊት ልጅ፥ የአብርሃም ልጅ</u> የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ» (ማቴዎስ 1፡ 1)

«<u>ኢየሱስም በይሁዳ ቤተልሔም... በተወለደ...</u> በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና...» (ማቴዎስ 2፡ 1፡ 5)

## <u>የመሢሑ አሟሟትም በነቢያት በኩል (በቶራኽና በዘቡር ከብዙ አስቀድሞ ተነግሮ ነበር</u>።

እዚህ ላይ ልታስተውለው የሚገባ ታላቅ ቁም ነገር ይኖራል። ለኃጢአተኛ ሲባል የንጹሑን ሕይወት ለሞት አሳልፎ በመስጠት መጀመሪያ ለዓለም ያስተዋወቀው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ይህም አዳምና ሔዋን ራሳቸውን በኃጢአት በበከሉበት ጊዜ እግዚአብሔር ለሁለቱም ኃጥአን የቁርበትን ልብስ ባለበሳቸው ጊዜ ነው
(ኦሪት ዘፍጥረት 3፡21)።

በኢየሩሳሌም በሞሪያ ተራራ ይሞታል
(ኦሪት ዘፍጥረት 22)። (2000 ዓ.ዓ.)

አሰቃቂ ሞት ይሞታል
(መዝሙረ ዳዊት 22)። (1000 ዓ.ዓ.)
ለሰው ልጅ ኃጢአት ሲል ይሞታል
(ኢሳይያስ 53)። (700 ዓ.ዓ.)
ከቤተ መቅደሱ መፈራረስ በፊት
ማለትም ከ70 ዓ.ዓ.) በፊት
ይሞታል (ዳንኤል 9፡25፥ 26)። (550 ዓ.ዓ.)

## <u>በኢንጅል የመሢሑ ሞት ተዘግቧል</u>

«አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ አቅርቦ እንዲህ አላቸው፡- እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ ስለ ሰው ልጅም በነቢያት የተጻፈው ሁሉ ይፈጸማል። ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታልና፥ ይዘብቱበትማል ያንገላቱትማል ይተፉበትማል፤ ከገረፉትም በኋላ ይገድሉታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል» (ሉቃስ 18፡31-33)።

«... አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ <u>ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር</u> አንድ ጊዜ ተገልጦአል» (ዕብራውያን 9፡26) ።



## <u>የመሢሑ ታላቅ ክብር በነቢያት በኩል በቶራኽ በዘቡር የተጻፈ አስቀድሞ ተነግሮ ነበር።</u>

በእባብ የተመሰለውን ሰይጣንን
ያሸንፋል (ዘፍ.3፡15)።

አሕዛብ ሁሉ የእግዚአብሔርን
በረከት የሚያገኙበት
መንገድ ይሆናል
(ኦሪት ዘፍጥረት 22፡18)። (2000 ዓ.ዓ.)

ከሞትም ይነሣል
(መዝ.16፡10) (1000 ዓ.ዓ.)
በእግዚአብሔር ቀኝ ይቀመጣል
(መዝሙረ ዳዊት [110]፡1)። (1000 ዓ.ዓ.)
የዘለዓለም ንግሥናን ይቀዳጃል
(መዝሙረ ዳዊት [89]፡35-37)። (1000 ዓ.ዓ.

## <u>በኢንጅል የተመዘገበ የመሢሑ ታላቅ ክብር</u>

ኢየሱስ ከሙታን ከተነ ሣ በኋላ ለሐዋርያቱ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፡-

«...ከእናንተ ጋር ሳለሁ <u>በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ</u> ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፡- <u>ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል</u>» (ሉቃስ 24፡44-47)።

## መሢሑን አስመልክቶ የተጻፉ የቁርአን ጥቅሶች

«መላእክት ያሉትን (አስታውስ):- መርየም ሆይ! አላህ ከርሱ በሆነው ቃል፥ ስሙ አልመሲሕ ዒሳ የመርየም ልጅ፥ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ፥ ከባለሟሎችም በኾነ (ልጅ) ያበስርሻል፤»

(ምዕራፍ 3 አሊ-ተምራን 45)።

«:- እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን በማለታቸውም፥ (ረገምናቸው)፤ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም፤ ግን ለነሱ (የተገደለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ፤ እነዚያም በርሱ ነገር የተለያዩት ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፤ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፤ በእርግጥም አልገደሉትም»

(ምዕራፍ 4 አል-ኒሳእ 157)።

«እላንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤ በአላህም ላይ እውነትን እንጅ አትናገሩ፤ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ፥ የአላህ መልክተኛ፥ ወደ መርየም የጣላት (የኹን) ቃሉና ከርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው፤ በአላህና በመልክተኞቹም እመኑ፤ (አማልክት) ሦስት ናቸው አትበሉም፤ ተከልከሉ፤ ለናንተ የተሻለ ይኾናልና፤ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለእርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው። በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው። መመኪያም በአላህ በቃ»

(ምዕራፍ 4 አል-ኒሳእ 171)።

«አልመሲሕ፥ ለአላህ ባሪያ ከመኾን ፈጽሞ አይጠየፍም፤ ቀራቢዎች የኾኑት መላእክትም (አይጠየፉም)፤ እርሱን ከመገዛት የሚጠየፍና የሚኮራም ሰው፥ (አላህ) ሁሉንም ወደ እርሱ በእርግጥ ይሰበስባቸዋል»

(ምዕራፍ 4 አል-ኒሳእ 172)።

«እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ፥ በእርግጥ ካዱ፤ የመርየምን ልጅ አልመሲሕን፥ እናቱንም፥ በምድር ያለንም ሁሉ ለማጥፋት ቢሻ፥ ከአላህ ማዳንን የሚችል ማነው? በላቸው። የሰማያትና የምድር፥ የመካከላቸውም ንግሥና የአላህ ብቻ ነው፤ የሚሻውን ይፈጥራል። አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው»

(ምዕራፍ 5 አል-ማኢዳህ 17)።

«እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ፥ በእርግጥ ካዱ፤ አልመሲሕም አለ:- የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ፤ እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው፥ አላህ በእርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ፤ መኖሪያውም እሳት ናት፤ ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም»

(ምዕራፍ 5 አል-ማኢዳህ 72)።

«የመርየም ልጅ አልመሲሕ፥ ከፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ፥ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም፤ እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፤ (ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ፤ አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሓዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት፤ ከዚያም (ከውነት) እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት»

ምዕራፍ 5 አል-ማኢዳህ 75)።

«አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው፥ አሉ፤ ክርስቲያኖችም አልመሲሕ የአላህ ልጅ ነው፥ አሉ፤ ይህ በአፎቻቸው (የሚናገሩት) ቃላቸው ነው፤ የነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ፤ አላህ ያጥፋቸው፤ (ከእውነት) እንዴት ይመለሳሉ?»

(ምዕራፍ 9 አል-ተውባህ 30)።

ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲኾኑ ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም፥ ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ፤ ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው»

(ምዕራፍ 9 አል-ተውባህ 31)።

ውድ አንባቢ፤-

ቁርአን ኢየሱስን በገሀድ ቃላት መሢሕ እንደሆነ ይገልጻል። ይሁንና መሢሕ የሚመጣ መሆኑን የሚያበስር ምንም ዓይነት ትንቢት እንደ ነበር አይጠቅስም፤ ስለዚህም መሢሕ የሚለው ቃል የቋጠረውን ትርጉም ለማብራራት አልሞከረም። ይሁንና ቁርአን ተውራት(ብሉይ ኪዳን) በራሱ በኢየሱስና በኢንጅል (ሐዲስ ኪዳን) የተረጋገጠ መጽሐፍ መሆኑ በግልጽ ያስቀምጣል።

«በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ፥ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን፥ አስከተልን፤ ኢንጅልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተ ፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ፥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሣጭ ሲኾን ሰጠነው»

(ምዕራፍ 5 አል-ማኢዳህ 46)።

ቁርአን ቀደምት የነበሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ይታመኑ ዘንድ ጽፎአል፡-

«እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና... ባወረደው መጽሐፍ፥ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ፤»

(ምዕራፍ 4 አል-ኒሳእ 136)።

በዚች ትንሽ መጽሐፍ በገጽ 2፥3 እና 4 የጠቀስናቸው ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ሊገኙ ይችላሉ። መጽሐፏን ማንበቡ እግዚአብሔር፥ በመሢሑ በኢየሱስ ላመኑ ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንደሚሰጥ ሊያስገነዝበን ይችላል።



ኢየሱስ በኢንጅል እንዲህ ብሎአል፡-

«...ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤ ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና። ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው። ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው» (ዮሐንስ 6፡37-40፥47)

ኢንጅል እንደገና የሚሰጠው ማረጋገጫ አለው፤ እንዲህም ይነበባል፡-

«ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤» (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15)።

«ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው። አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥» (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡4-6)።

«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

«ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)።

«በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» (ፊልጵስዩስ 2፡9-11)።

ልብ በል፡- መሢሐ ኢየሱስን እንደ አዳኝህና ጌታህ ትቀበለው ዘንድ እግዚአብሔር ፈቃዱ ነው። ኢየሱስን እንደ አዳኝህ በተቀበልህ ጊዜ ለኃጢአትህ ሁሉ ይቅርታን ታገኛለህ። እግዚአብሔርም ሰማያዊ አባትህ እንደሆነ ትረዳለህ። መንግሥተ ሰማይም የምትገባበት ዋስትና ይኖርሃል። መሢሐ ኢየሱስን እንደ አዳኝህ ለመቀበል ቁርጠኛ ፍላጎት ካደረግህ የሚከተለውን ጸሎት መጸለይ ትችላለህ። እግዚአብሔርም ይሰማሃል።

ኃያሉ እግዚአብሔር ሆይ፥ መሢሐ ኢየሱስ እንደሚወለድ፥ ለሥቃይና ለሞትም እንደሚዳረግና የሚጎናጸፈውን ታላቅ ክብር ሁሉ በመግለጽ ወደ ዓለም ከመምጣቱ ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምረው ነቢያት እንዲጽፉ ስላደረግህ አመሰግንሃለሁ። በመሢሐ ኢየሱስ በኩልም ለእኔ ያለህን ፍቅር ስለ ገለጽክልኝ በጣም አመሰግንሃለሁ። ለኃጢአቴ ስርየት መሢሐ ኢየሱስ ራሱን ለሞት አሳልፎ እንዲሰጥ ስላደረግክ አመሰግንሃለሁ። የዘለዓለምን ሕይወት እጎናጸፍ ዘንድ መሢሐ ኢየሱስን ከሞት ስላስነሣኸው አመሰግንሃለሁ። ኃጢአተኛ መሆኔን ጠንቅቄ አውቃለሁ። ኃጢአቴን ይቅር ትለኝ ዘንድም እለምንሃለሁ። ለእኔ ሲል ሕይወቱን ለሞት አሳልፎ በሰጠው በመሢሐ ኢየሱስ ምክንያት ያገኘሁትን የኃጢአት ስርየት በዚችው ደቂቃ እቀበላለሁ። መሢሐ ኢየሱስ ጌታዬ ይሆን ዘንድ ፍላጎቴ ነው። ኢየሱስ ለሁሉ ያለውን ፍቅር ያህል እኔም ሌሎችን እወድ ዘንድ የዘለዓለም እርዳታህ አይለየኝ። ከኃጢአቴ ስላነጻኸኝ አመሰግንሃለሁ። ስለተቀበልከኝም አመሰግንሃለሁ። ይህን ሁሉ ጌታዬና አዳኜ በሆነው በመሢሐ ኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ፤ አሜን።